# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርቡ ፕሮግራማችን ወንድማችን ሲሳይ ስለ ጸጋ እያስተማረን ነው። እንዲሁም በልዩ ልይ ጉዳዮች ላይ እንጸልያለን። የምትችሉ ሁሉ እንድትካፈሉ እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ **በNovember 19 ወይንም እስከ አመቱ መጨረሻ** (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። ፎርሙን ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች ደግም እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው። እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?


ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




## "...እኔ ግን በእግዚአብሐር ደስ ይለኛል..."

(ዕም. 3፡18)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**November 5, 2017**

**ጥቅምት 26፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| ቃል ........................... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

"ጌታ እግዚአብሔር ኃይሌ ነው፤ እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፤ በከፍታዎችም ላይ ያስሄደኛል።"

(ዕም. 3፡ 19)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኀ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- መንግስትህ ትምጣ —ደስታ (ክፍል ስምንት)**

*"እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>መንግስትህ ትምጣ</u> ..." (ሉቃ. 11፡1-2)*

መንግስትህ ትምጣ ብለን ስንጸልይ እየፈልግን ያለነው የግዚአብሔርን ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሚሆንን ደስታ ነው። (ሮሜ 14፡17) ባለፉት ሁለት ሳምንታት ጽድቅና ሰላም የሚሉትን ሃሳቦች አይተናል። ዛሬ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግስት በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ደስታ ናት በሚለው ሃሳብ ላይ እናተኩራለን።

የእግዚአብሔርን መንግስት በመፈለግ ጸሎት ውስጥ የሚጠቃለለው አንዱ ሃሳብ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆንን ደስታ መፈለግ ነው። መንግስቱን ስንፈልግ እግዚአብሔር ደስታን ይሰጠናል። ሰዎች በሚያገኙት ነገር ለተወሰነ ጊዜ ደስ ሊሰጣቸው ይችላል። ነገር ግን በብዙ ጥረትና ድካም የተገኘ ነገር ለጊዜው ደስ ቢያሰኝም እንኳን ወረቱ ሲያልፍ በሌላ ምኞት ይተካና ያመጣው ደስታ ይደበዝዛል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች ለመደሰት ሲሉ የተለያየ ሱስና የሃጢያት ልምምድ ውስጥ ይገባሉ። ነገር ግን ይህም ቢሆን ለጊዜው የሚሰጠው ደስታ ሲያልፍ ትርፉ ጸጸትና ራስ ምታት ይሆናል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ደስታ ምንጩ መንፈስ ቅዱስ ነው። ደስታው ከውስጥ የሚወጣ እንጂ በውጪ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ አይደለም። ደስታችን መሰረቱ የሚመጡና የሚሄዱ ጉዳዮች ሳይሆኑ እግዚአብሔር እራሱ ነው። ለዚህ ነው እምባቆም "ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ" በማለት የተቀኘው። (ዕም. 3፡17-18) እምባቆም በውጫዊ ነገሮች መጉደል ተናውጦና ደስታ ርቆት ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርን በክብሩ ከተመለከተ በኋላ አንድ እውነት በራለት። ለካስ የደስታ ምንጩ እግዚአብሔር እንጂ የመሙላትና የመጉደል ጉዳይ አይደለም። እግዚአብሔር ደስታን ያልሰጠው ሰው ሁሉ ሞልቶትም እንኳ እርካታን ያጣል። ለዚህ ነው መጽሐፍ "ያለ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሰ ማን ነው?" (መክ. 2፡25) የሚለን። ከርሱ ውጪ ደስታ የለም። ሰለሞንም ሁሉን ፈትኖ ደስታን ከሰበሰበው ሃብት፣ ጥበብ፣ ዝናና ተድላ ውስጥ ቢያጣት ጊዜ እግዚአብሔር "ደስ ለሚያሰኘው ሰው ጥበብንና እውቀትን ደስታንም ይሰጠዋል" (መክ. 2፡26) በማለት የእውነተኛ ደስታ ምንጩ እርሱ እንደሆነ ተናገረ።

ወገኖቼ፦ ሰው ብዙ የሚደክመው ለመደሰት ነው። ነገር ግን ለሰው የውስጥ ደስታን የሚሰጠው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ የሚሰጠን ደስታ ኃይላችን ነው። (ነህ. 8፡10) በመንግስቱ ውስጥ ደስታ አለ። እግዚአብሔር ሆይ መንግስትህ ትምጣ። አሜን!